# መጽሐፍ ቅዱስ ይጣረሳልን?

አንዋር መሐመድ

ለአህመድ ዲዳትና ለሌሎች ሙስሊም ምሁራን ጥያቄዎች የተሰጠ መልስ

አሳታሚ፡- ጌጃ ቃለ ሕይወት ሥነጽሑፍ አገልግሎት
ፖ.ሣ.ቁ.698 ፣ስልክ 76 33 28/ 76 98 30
E-mail hiwotlit@telecom.net.et.

መጋቢት 1997 ዓ/ም

# መግቢያ

ይህ መጽሐፍ የተዘጋጀበት ዓላማ አንዳንድ ሰዎች ስለመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ጥርጣሬ ውስጥ ስለገቡ መጽሐፍ ቅዱስን በተመለከተ እውነቱ ምን እንደሆነ ለማሳየት ነው::እንደዚሁም በሚስተር አህመድ ዲዳት እና ሌሎች ሙስሊም ምሁራን የሚቀርቡትንም ጥያቄዎች መጽሐፍ ቅዱስን መሠረት ባደረገና ቁርአንን ባገናዘበ መልኩ መልስ ተሰጥቶባቸዋል::

መጽሐፉ ሁለት ዋና ዋና ክፍሎች አሉት:: አንደኛው ስለመ ጽሐፍ ቅዱስ መበላሸት የሚነሱት የተለያዩ ተቃዎሞዎች መልስ የሚሰጥ ሲሆን ሁለተኛው መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጋጫል ለሚለው የተሳሳተ አመለካከት የመጽሐፍ ቅዱስን የአጠናን ዘዴ መሠረት በማድረግ ይጋጫሉ ተብለው የሚቀርቡትን ጥቅሶች ማብ ራሪያ ይሰጣል::

ይህንን መጽሐፉ በማንበብ አንዳንድ ሰዎች ከተለያየ አቅጣጫ የሰሙትን ወይንም መጽሐፍትን በማንበብ ያገኙትን የተሳሳተ ግንዛበ፣ እንዲያስተካክሉና የመጽሐፍ ቅዱስን እውነተኛነትና ሕያውነት እዲረዱ ያግዛቸዋል የሚል ተስፋ አለኝ:: መጽሐፉ በተለያየ የእምነት ቡድን ውስጥ ላሉ ሰዎች፣ ለመጽሐፍ ቅዱስ ት/ቤት ተማሪዎችና ለሌሎችም ጠቃሚ እንደሚሆን ተስፋ አደርጋለሁ::

©Anwar Mohammed,2005
First edition March,2005
የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው::
All Rights Reserved.

Published by Heywet Literature
P.o.Box 698
E-mail hiwotlit@telecom.net.et.
Addis Ababa, Ethiopia

# ማውጫ

## ርዕስ                    ገጽ


ምዕራፍ አንድ ———————— 1-6
**መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን?**

ምዕራፍ ሁለት ———————— 7-21
**መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቷልን?**

ሀ/ የቁርአን እና ሙስሊም ሊቃውንቶች ምስክርነት
ለ/ ታሪካዊ መረጃዎች
ሐ/ ከአራትና ከወንጌላት ውጪ ሌሎች መጽሐፍት የመ
ጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አይደሉምን?
መ/ የበርናባስ ወንጌል ትክክለኛ ወንጌል ነውን?

ምዕራፍ ሦስት ———————— 22-33
**መጽሐፍ ቅዱስና ሚስተር አህመድ ዲዳት**

ሀ/ ሦስት ዓይነት ንግግሮች
ለ/ የተለያዩ ትርጉም መጽሐፍት
ሐ/ 50,000 ስህተት በመጽሐፍ ቅዱስ
መ/ ከአራት ሺህ መጽሐፍት አራት ወንጌላት ብቻ
ሠ/ አሳፋሪ ታሪኮች በመጽሐፍ ቅዱስ
ረ/ የኢየሱስ የዘር ሐረግ ግጭት

ምዕራፍ አራት ———————— 34-79
**መጽሐፍ ቅዱስ እርስ በርሱ ይጋጫልን?**

የሰው ሕይወት ምንድነው? ለሚለው ጥያቄ መልሱን እኔ አውቃለሁ የሚሉ ብዙ ግብታዊና ስሜታዊ ደፋር ተንታኞች በዓለም ሁሉ ሞልተዋል::ብዙ መጻሕፍትም ጽፈዋል:: ሆኖም በዓለም ያሉ ብዙ ሰዎች በእነዚያ ትንተና ሁለጭና ስለሕይወት ምንነት መገለጫ በተጻፉት መጻሕፍት አልረኩም:: የሰውን የልብ ጥያቄ እንዲህ በቀላሉ እኔ አውልሃለሁ በሚል ዲስኩር ማርካት ፈጽሞ አይቻልም:: ምሁር ወጣት አንዋር ግን ገና በወጣትነቱ ቁርዓንንና ሌሎችንም መጻሕፍት በጥልቀት አጥንቶ በኋላም ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር በማነጻጸር የእግዚአብሔርን ማንነት፣የሰውን ምንነት ፣የሕይወትንም መነሻና ግብ ያረጋገጠ ወጣት ነው::

ይህንንም "መጽሐፍ ቅዱስ ይጣረሳልን?" በሚል ርዕስ የጻፈውን መጽሐፍ ያቀረበው እሱን ለመሰሉ ወጣቶችና ለጎልማሶችም ለአዛውንቶችም እውነትን በግልጽነት ሁሉ እንዲመለከቱ ነው:: ስለዚህ ማንም ሰው በተለይም አንዳንዶች በፍርሃት በሥጋትና በይሉኝታ ተገድበው ሳያምኑ ይህንን በበሰለ ጥናታዊ መረጃና በግልጽ ተግባራዊ የሕይወት ግንዛቤ ተዘጋጅቶ የቀረበውን መጽሐፍ እንዲያነቡ አሳስባለሁ::

ኩርሲ ሽፈና
የኢትዮጵያ ቃለ ሕይወት ቤተክርስቲያን
ም/ ዋና ፀሐፊ

የወንድማችን አንዋር መሐመድ ሥራ እጅግ በጣም ጥሩ ነው:: በዋናነት ከሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች በተደጋጋሚ የሚሰነዘሩትን ትችቶች መስመር የሚያስይዝና የሚከላከልም ሲሆን በመጽሐፉ ውስጥ የተነሱት ነጥቦች ደግሞ በተጨባጭ በአገራችን በሌሎች የሚነሱትን ነጥቦች መልስ የሚሰጥ በመሆኑ ለየት ያደርገዋል::

መጽሐፉ ሰዎች መጽሐፍ ቅዱስ ለመተርጎም መከተል ያለባቸውን መርሆዎች (Principles) ጭምር በማንሳት አንዳንድ ብዥታዎችን ከማስወገድም አንጻር ጠቃሚነት ያለው በመሆኑ አማኞችም ሆነ እውነትን የሚፈልጉ ሁሉ ቢያነቡት ይጠቀሙበታል::

ሽፈራው ሰዒድ
የኢትዮጵያ ወንጌላውያን አብያተክርስቲያናት
ሕብረት የልዩ ሃይማኖቶች ጥናት አስተባባሪ

ይህ በወንድም አንዋር መሐመድ የተዘጋጀው መጽሐፍ በእስልምና እና በክርስትና መካከል እየተደረገ ስላለው ውይይት በጣም ጠቃሚ አስተዋጽኦ አለው:: እናንብበው፣ እንጠቀምበት!

ምሕረቱ ጴ.ጉታ
የመልስ ይኖረው ይሆን? መጽሐፍ ፀሐፊ

ዶ/ር አህመድ ዲዳት በርካታ የተሳሳቱ አስተያየቶችን በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ በመሰንዘር፣ ብዙዎችን በማደናገር ላይ ይገኛሉ:: ወንድማችን አንዋር መሐመድ በብዙ ጥንቃቄ መጽሐፍ ቅዱስን በማጥናት ለእኚህ ሰው የተሳሳቱ አመለካከቶች ምላሽ የሚሆኑ መልሶችን አዘጋጅቷል:: ለብዙዎች ግራ መጋባት በቂ ምላሽ ያለው ጽሑፍ እንደሆነ እንተማመንበታለን::

የሕይወት መጽሔት

# ምዕራፍ አንድ

## 1/ መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃል ነውን?

ማንኛውንም የሃይማኖት መጽሐፍ እውነተኛ ወይንም ሐሰተኛ የሚያሰኘው ምንጩ ነው:: የመጽሐፉ ትክክለኛነት የሚለካው በእጅ ብልጫ ወይንም በደጋፊዎች ጥንካሬ አይደለም:: እንዲህ ቢሆን ኖሮ ፈተናውን የሚያልፉ አእላፋት መንፈሳዊና ዓለማዊ ጽሑፎች እንደሚኖሩ ተስፋ አደርጋለሁ:: የእውነት ሕልውና በተከታይ ብዛት ወይንም በጭብጨባ አይጠ ረጋገጥም:: በተቃራኒው የተቃውሞ መብዛት እውነትን አያጠ ውም:: የእውነት ምንጭና መሠረት ፈጣሪ እግዚአብሔር ነው:: ፈጣሪ ራሱ የእውነት አምላክ ነው:: ሐሰትንም ይጸየፋል:: ፈቃዱንና ማንነቱንም የገለጠው እውነተኛና ዘለዓለማዊ በሆነው ቃሉ በኩል ነው:: ቃሉም የተገለጠው በመላዕክት ቋንቋ ሳይሆን ሰዎች ሊገባቸውና ሊረዱት በሚችሉት በራሳቸው ቋንቋና ባህል ውስጥ ነው:: ይህም ከጥንት ጀምሮ በሰዎች ታሪክ ውስጥ ጣልቃ እየገባ ተአምራትን ሲያደርግ፣ ሕዝቡን ከተለያየ መከራ ሲያድን፣ ሐጢአተኞችን ሲቀጣ፣ ፈቃዱን ሲያስታውቅ እና ስለ ማንነቱ በቅዱሳን ሰዎች አማካይነት ሲናገር ቆይቷል:: ዕብ.1:1-2 እንዲህ ይላል " ከጥንት ጀምሮ እግዚአብሔር በብዙ ዓይነትና በብዙ ጎዳና ለአባቶች በነብያት ተናግሮ ሁሉን ወራሽ ባደረገው ደግሞም ዓለማትን በፈጠረበት ብልጁ በዚህ ዘመን መጨረሻ ለእኛ ተናገረን:: " ይህንንም ቅዱሳን ነብያትና ሐዋርያት ጽፈው ለሌሎች እንዲያስተላልፉ አድርጓል:: ከዚህም የተነሳ መጽሐፍ ቅዱሳችን እግዚአብሔር በታሪክ ውስጥ ጣልቃ እየገባ የሰራቸውን ስራዎች፣ ፈቃዱን፣ ስለማንነቱ እንዲሁም የተለያዩ ሰዎችን ታሪክ፣ ንግግሮችና ትምሕርቶች የያዘ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ ስለራሱ ምንጭ እና እንዴት እንደተገለጠ ሲገልጽ እንዲህ ይላል:- «ይህን በመጀመሪያ እወቁ በመጽሐፍት ያለውን ትንቢት ሁሉ ማንም ለገዛ ራሱ ሊተረጉም

አልተፈቀደም፤ ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።» 2ጴጥ.1፡20-21። ይህ ክፍል እንደሚያስተምረው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለው ትምሕርት በአጠቃላይ የሰዎች ፈጠራ ሳይሆን በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት ቅዱሳን ሰዎች የጻፉት የፈጣሪ ፈቃድና ሐሳብ ነው። የተለያዩ ሰዎች በዘመናቸው የዓለምን ሁኔታ በመመልከት የራሳቸው የሆኑ ጽሑፎችን ደርሰዋል። ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል ከዚህ ፍጹም የተለየ ነው። ዓላማውም «የእግዚአብሔር ሰው ፍጹምና ለበጎ ሥራ ሁሉ የተዘጋጀ» እንዲሆን ማድረግ ነው። 2ጢሞ.3፡16 በቁጥር 17 ላይም በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉት መጽሐፍት በሙሉ «ለትምሕርትና ለተግሣጽ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ደግሞ ይጠቅማል።» ይላል። ዳዊት በመዝሙር «ሕግህ ለእግሬ መብራት ለመንገዴ ብርሃን ነው» መዝ.119፡105 ሲል ጽፎአል።

ቁርዓንም ስለመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭና ተግባር ተመሳሳይ መግለጫ ይሰጣል። የመጽሐፍ ቅዱስ ምንጭ ፈጣሪ አምላክ ብቻ እንደሆነና ጸሐፊዎቹም ቅዱሳን ሰዎች እንደሆኑ ከ2ኛ ጴጥ.1፡20-21 ጋር ይስማማል። መልዕክቱም የተላከው በአንድ ነብይ አማካይነት እንዳልሆነ ነገር ግን በብዙ ቅዱሳን በኩል እንደሆነ በተደጋጋሚ ያስተምራል። ይህንን ሐሳብ በሱራ 5፡44 እንዲህ ይገልጸዋል። «እኛ ተውራትን በውስጥዋ መመሪያና ብርሃን ያለባት ስትሆን አወረድን፤ እነዚያ ትዕዛዝን የተቀበሉት ነብያት በነዚያ ይሁዳውያን በኾኑት ላይ በርሷ ይፈርዳሉ፤...።» በዚህ የቁርዓን ጥቅስ ሦስት ዋና ዋና ነገሮች እናገኛለን። 1ኛ/ ተውራት የሰው ፈጠራ ሳይሆን የፈጣሪ መልዕክት ነው። 2ኛ/መመሪያና ብርሃን በውስጡ አለበት። ታዋቂው የእስልምና ሊቅ አብደላህ የሱፍ አሊ ሲያብራራው «መመሪያ» ማለት ሰዎች ትክክለኛና እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝ ባሕሪይ እንዲኖራቸው ትምህርት ይሰጣል። «ብርሃን» የሚለው ሐሳብ ደግሞ ስለመንፈሳዊው ዓለም ትክክለኛ እውቀት ያስጨብጣል ሲል ገልጦታል። (Holy Quran,page.261) ይህም በ2ጢሞ.3፡16-17 እና መዝ. 119፡105 ላይ ካሉት ሐሳቦች ጋር ተመሳሳይ ነው። 3ኛ/ መልዕክቱ የተገለጠው ነብያቱ ወይንም የሃይማኖት ሊቃውንቱ

በተገለጠው ሕግ መሠረት እንዲፈርዱ ወይንም ሃይማታዊ መመሪያ ይሰጡ ዘንድ ነው::

በሱራ5:46 ኢንጂልን /ወንጌላትን/ ለተመሳሳይ ዓላማ እና ተግባር እንደተላከ ያሳስባል:: ወንጌላትንም ስለ ብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ትክክለኛነትና ስልጣን ምስክርነት የሚሰጡ ናቸው::

በተመሳሳይ ሁኔታ ከቁርዓን ተግባሮች አንዱ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት ማረጋገጫ መስጠት ነው:: በሱራ 5:48 እንዲህ ይላል:- «ወደ አንተም መጽሐፉን ከበፊቱ ያለውን መጽሐፍ አረጋጋጭና በእርሱ ላይ ተጠባባቂ ሲሆን በእውነት አወረድን፤ ...::» በዚህ ክፍል «መሐይሚን» የሚል የዐረብኛ ቃል «አረጋጋጭ» የሚለውን ሐሳብ ይገልጻል:: በአውዱ መሠረት «ምስክርነትን መስጠት» የሚል ትርጉም አለው:: ስለዚህ የቁርዓን ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን መሻር ወይንም መቃወም ሳይሆን ስለ እውነተኛነቱ ምስክርነት መስጠት ነው:: ለዚህም ነው በነብዩ መሐመድ ዘመን ትክክለኛ ፍርድና መመሪያ ፈልገው ወደ ነብዩ የመጡትን አይሁዶች እንዲህ በማለት ነበር የመለሰዋቸው:- «እነርሱ ዘንድ ተውራት እያለች በውስጧ የአላህ ፍርድ ያለባት ስትሆን እንዴት ያስፈርዱሃል ከዚያም ከዚህ በኋላ እንዴት ይሸሻሉ. እነዚያ በፍጹም ምዕመናን አይደሉም::» ሱራ 5:43 ክርስቲያኖችም ሆኑ አይሁዶች በእጃቸው ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ እውነት እያላቸው ሌላ መፈለግ አይገባቸውም:: ለወደፊትም ቢሆን በተሰጣቸው መጽሐፍ መመሪያ መሠረት እንዲኖሩም በሱራ 5:47 ያስጠንቅቃል:: መጽሐፍ ቅዱስ ክርስቲያኖችና አይሁዶች ብቻ የሚጠቀሙት ሳይሆን ሙስሊሞችም እንዲያምኑበት ሱራ 2:136 ለሙስሊሞች እንዲህ ሲል ማሳሰቢያ ይሰጣል:-" በአላህና ወደኛ በወረደው /ቁርዓን/ ወደ ኢብራሂምም፣ ወደ ኢስማዒልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቆብና ወገነገዶቹም በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያቱም ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት ከነርሱ በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን፤..." ይህ ክፍል የመጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛት ማመንና መቀበል እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው::

መጽሐፍ ቅዱስ በ1500 ዓመታት ጊዜ ውስጥ በተለያየ ቦታና ዘመን በኖሩ ከ40 በላይ ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው:: እጅግ ጥልቅ ትምሕርቶች በውስጡ የያዘ ከመሆኑም በላይ ያለ ምንም ዓይነት መዛነፍ እና ግጭት አንድነቱን ጠብቆ ይኖራል:: የሰው አእምሮ ፈጠራ ቢሆን ኖሮ የአንደኛው ጸሐፊ ትምሕርት ከሌላኛው ጋር በተቃረነ ነበር:: ነገር ግን ምንጩ ፈጣሪ አምላክ ስለሆነ ሁሉንም

ሁኔታዎች በበላይነት በመቆጣጠር እግዚአብሔር ስለፈቃዱና ማንንቱ ያለምንም እንከን እንዲጸፍና ለትውልድም እንዲተላለፍ አድርጓል:: ከዚህም የተነሳ አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር ለቅዱሳን ሰዎች የገለጠውን መልዕክት ያለምንም ጭማሪና ቅናሽ የያዘ ነው:: የአምላካችን ቃል ብዙ ዘመናት ቢያልፍም፣ ሊያጠፉት የተነሱ አያሌ ጠላቶች ቢኖሩ በትም፣ የሚያንቋሽሹት አእላፋት ተቃዋ ሚዎች ቢገጥሙትም ያለ ማንም ድጋፍ በራሱ እያሸነፈ ዛሬ እስካለንበት ደርሶአል፤ ወደፊትም ይቀጥላል:: አሁንም እነዚህም ተግዳሮቶች ጠፍተዋል ማለት አይደለም:: ነገር ግን ሕያው እውነት ስለሆነ ሁሌም እያሸነፈ ለዘላለም ይኖራል::

በመጽሐፍ ቅዱስ ዕብ.4:12 ይህንን እውነት እንዲህ ይገልጠዋል::«የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነውና፣ የሚሠራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ሁሉ ይልቅ የተሳለ ነው::... » አዎ የእግዚአብሔር ቃል የማይሻር፣የማይሻሻል ወይንም የማይለወጥ የሁሉን ቻይ አምላክ እስትንፋስ ነው:: ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለ እግዚአብሔር ቃል ሲናገር « እኔ ሕግንና ነብያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም:: እውነት እላችኋለሁ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ ከሕግ አንዲት የወጣ ወይንም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም ሁሉ እስኪፈ ጸም ድረስ::» /ማቴ.5:17-18/ ጌታ ኢየሱስ ይህንን መልዕክት በማቴ.24:35 እና በዮሐ.10:35 ደግሞታል:: እግዚ አብሔር ዘመን ሲለዋወጥ ሐሳቡ አይለዋወጥም:: ከኋላ የመጣው ነብይ የበፊቱን

መልዕክት አይቀይርም:: ነብዩ ኢሳይያስ በኢሳ.40:8 «ሣሩ ይደርቃል አበባውም ይረግፋል የአምላካችን ቃል ግን ለዘላለም ጸንታ ትኖራለች::» ብሏል:: በዘመናችን አንዳንድ ሰዎች እንደሚያስቡት የእግዚአብሔር ቃል የተለወጠ፣ የተበላሸ ወይንም በሌላ መገለጥ የተተካ አይደለም:: ቀደም ብለን እንደተመ ለከትነው ቁርዓንም ይሁን መጽሐፍ ቅዱስ እንደሚያረጋግጡት መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር ቃልና ለዘለዓለም ያለብልሽት ጸንቶ የሚኖር ነው::

በሌላ አንጻር ግን ሐሰተኛ ነብያቶች ወይንም አስተ ማሪዎች ሊነሱና ልዩ ልዩ መጽሐፍት ሊጽፉ ይችላሉ:: እንደ ዚህ ዓይነት ሰዎች ጥንትም ነበሩ ዛሬም ይኖራሉ:: ነገር ግን እውነተኛው ከሐሰተኛው በምን እንለያለን የሚል ጥያቄ መነሳቱ አግባብነት ያለው ይመስለኛል:: ለዚህም ጥያቄ የእግዚአብሔር ቃል መልስ አለው:: ገላ.1:8-9 እንዲህ ይነበባል:: «ነገር ግን እኛ ብንሆን ወይንም ከሰማይ መላዕክት ከሰበክንላችሁ ወንጌል የሚለይ ወንጌልን ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን:: አስቀድመን እንዳልን እንዲሁ አሁን ሁለተኛ እላለሁ፣ ከተቀበላችሁት የተለየውን ማንም ቢሰብክላችሁ የተረገመ ይሁን::» በዚህ ክፍል ወንጌል ማለት «የምስ ራቹ ቃል » ማለት ነው:: መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛውን ከሐ ሰተኛው የምንለይበት ጥሩ መመዘኛ ሰጥቶናል:: ስለዚህ ማንኛውም ሐዋሪያም ይሁን ነብይ ነኝ ባይ ከቀድሞ ነብያትና ሐዋርያት የተለየ ትምሕርት ካስተማረ ወይም ከጻፈ ሐሰተኛ ነው:: በእርሱ የተጻፈ መጽሐፍም ካለ የሚመዘነው በውስጡ በያዘው ትምሕርትና ምንጩን ባገናዘበ መልኩ ነው:: ቁርዓንም ሆነ የነብዩ መሐመድ ትምሕርት ከቀድሞ ነብያቶች ትምሕርት የተለየ ከሆነ ሊፈተሽ ይገባዋል::ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሞቱና ትንሳኤው ለሐዋርያቱ ሲያስተምር ሐዋርያው ጴጥሮስ የክርስቶስን ሞት በተቃወመ ጊዜ ጌታ የመለሰለት "ወደ ኋላዬ ሂድ አንተ ሰይጣን የሰውን እንጂ የእግዚአብሔርን ነገር አታስብምና አለው::" ከዚህ ክፍል የምንረዳው የክርስቶስን ሞትና ትንሳኤ መቃወም ሐሰኛነት ከመሆኑም በላይ የሰይጣንን ሐሳብ አስተናጋጅነትን ነው:: እውነተኛውን መንገድ ለመረዳት መሠረት

ማድረግ ያለብን የቀድሞ ነብያት ፣የክርስቶስና የሐዋርያት ትምሕርት ነው:: ዛሬም የክርስቶስን ትምህርት ተቃውሞ የሚያስተምር ወይንም መጽሐፍት የሚጽፍ ራሱም መጽሐፉም ሐሰተኛ ነው:: ማንኛችንም በዚህ መስፈርት የራሳችንን ጥናት ልናደርግና እውነተኛውን መንገድ ልንከተል አሊያም በእውነተኛው መንገድ ያለን አጥብቀን ልንይዝ ይገባናል::

አሁንም ደግሜ እላለሁ ፣ፈጣሪ አምላክ ተቃራኒ መልዕክቶች ለመልዕክተኞቹ አይሰጥም:: ይልቁንም የአንዱ ነብይ ትምሕርት ከበፊቱ ከነበሩት ተመሳሳይ ወይንም የቀድሞውን የሚያጠናክር ነው:: የበፊቱን የሚያፈርስ ከሆነ ያለምንም ጥርጣሬ ሐሰተኛ ትምሕርት መሆኑ ይታወቃል::

ሰዎች በራሳቸው ጊዜ ተነስተው የመሰላቸውን ሊያስተምሩ ይችላሉ:: ነገር ግን የእግዚአብሔር ቃል በዘዳ.17:6 እንደሚናገር ቢያንስ የሁለት ወይንም የሦስት ቅዱሳን ምስክርነት አስፈላጊ ነው:: ትምሕርቱም ከእግዚአብሔር ስለመላኩ በቂ መረጃ ሊኖር ይገባል:: ያለምንም ማጣሪያ ሰዎችን ከፈጣሪ እንደተላኩ አድርገን የምንቀበል

ከሆነ ዛሬም ነብይ ነኝ ብሎ የመጣን ሁሉ መቀበላችን አይቀሬ ነው:: ስለዚህ ማንኛችንም ክርስቲያንም ሆንን ሙስሊም ለምናደርጋቸው መንፈሳዊ ውሳኔዎች ልንጠነቀቅ ያስፈልገናል:: ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ ያሉትን መጽሐፍት ምንጫቸውንና ትምሕርታቸውን መርምረን መጣል ያለብንን መጣል ይገባናል:: ከእግዚአብሔር ቃል ውጪ የምናደርጋቸው ውሳኔዎች ሁሉ የሞትና የሕይወት ምርጫ ስለሆኑ እንጠንቀቅ:: ምክንያቱም እውነተኛውን የደህንነት መንገድ ከመረጥን የዘለዓለም ሕይወት፣ ከተሳሳትንም የዘላለም ሞት በፊታችን ነውና::

# ምዕራፍ ሁለት
## መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቷልን?

መጽሐፍ ቅዱስ ተበላሽቷል የሚለው ተቃውሞ በአንዳንድ ሙስሊሞች ወገኖቻችን ዘንድ ይደመጣል:: ተበላሽቶ እንደሆነ ወይንም እንዳልሆነ የተለያዩ መረጃዎችን መዳሰስ አስፈላጊ ነው:: ከዚህ ቀጥሎ የቁርዓንን የመጽሐፍ ቅዱስና ሌሎችንም መረጃዎች ሚዛናዊ በሆነ መንገድ እንመልከት::

### ሀ/ የቁርዓንና የሙስሊም ሊቃውንቶች ምስክርነት

### ቁርዓን እና ሙስሊም ሊቃውንቶች ስለመጽሐፍ ቅዱስ መበላሸት ምን ያስተምራሉ?

ቀደም ብዬ መጽሐፍ ቅዱስ ከእግዚአብሔር ዘንድ የተሰጠ መለኮታዊ መገለጥ እንደሆነ የቁርዓን ጥቅሶችን በመውሰድ ለማብራራት ሞክሬአለሁ:: በነብዩ መሐመድ ዘመን የነበረው መጽሐፍም እውነተኛና ያልተበረዘ እንዲሁም አይሁዶችና ክርስቲያኖች በዚያ መጽሐፍ ሕግ መሠረት እንዲኖሩ ቁርዓን ሲያዛቸው እንመለከታለን:: /ሱራ5:44-47/ በ7ኛው ክፍለ ዘመን የነበረው መጽሐፍ ቅዱስ እንከን እንዳልነበረበት ከቁርዓን አንቀጾቹ መረዳት እንችላለን:: ወደፊትም እንደማይለወጥ ቁርዓን በአንክሮ ያስገ ነዝባል:: ምክንያቱም ቃሉን ከብልሽትና ከስህተት የሚጠብቅ ፈጣሪ አምላክ ራሱ ነውና ሱራ 22:52

የጥንት ሙስሊም ሊቃውንቶችም ከዚህ ጋር ተመሳሳይ አመለካከት አላቸው:: ከእነዚህም ውስጥ በጣም የተከበሩና በሙስሊሙ ሕብረተሰብ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነት ያላቸው ሙስሊም ሊቃውንት አቋም እንደሚከተለው ነው፣ አል-ታባሪ የተባለ እውቅ

ሙስሊም የታሪክ ጸሐፊ በእርሱ ዘመን በአይሁዶችና በክርስቲያኖች እጅ ያለው መጽሐፍ እንከን የሌለበትና ከጥንቱ መጽሐፍም ጋር አንድ እንደሆነ ተቀብሎአል:: እንዲሁም በ1209ዓ.ም የሞተው ፋህሩ ዲን ራዚ የተባለው ሙስሊም ፋሎስፈርና የቁርዓን ሊቅ ስለ እግዚአብሔር ቃል እውነተኛነትና ስልጣን ተቀብሎአል:: በተጨማሪም አቡ ሐሚድ አል-ጋዛሊ የተሰኘው ታዋቂው ሙስሊም የሥነ-መለኮት ሊቅ በእርሱ ዘመን መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃወሙ ሰዎች ቢኖሩም ስለክርስቲያኖች መጽሐፍ እውነተኛነት በሰፊው አትቷል::

እየዋለ እያደር ግን ጥቂት ሙስሊሞች ቁርዓን የማያስተምረውና ቀደም ብለን የተመለከትናቸው የቀድሞዎቹ የእስልምና አስተማሪዎች ያላስተማሩትን ትምሕርት ማስተማር ጀምረዋል:: ለዚህም እንቅስቃሴ መጀመር መሪ ተዋናይ በ11ኛው ክፍለ ዘመን የኖረው ኢብን ሐዝም የተባለ ሰው ነው:: ይህ ሰው የክርስትና እምነትን ብቻ ሳይሆን የተለያዩ የእስልምና ቡድኖችንም በመቃወም ጽፎአል:: በመሠረቱ ሚዛና ዊነት የጎደለው ሥራ እንደ ሠራ ሥራዎቹ ምስክሮች ናቸው:: በአሁንም ዘመን እነአህመድ ዲዳት የዚያን ሰው ፈለግ በመከተል መሠረተ ቢስ ተቃውሞዎቹ ቀጥለዋል:: ንጹህ ሕሊና ያላቸው ሙስሊሞች ባይቀበሉትም አንዳንዶች በግብታዊነት መረጃን መሠረት ባላደረገ መልኩ መጽሐፍ ቅዱስን ያንቋሽሻሉ:: ቁርዓን የመጽሐፍ ቅዱስን በጽሑፍ ደረጃ መበላሸት ያስተምራል ሲሉም ይከራከራሉ:: ነገር ግን ይህ ተቃውሞ እውነተኛነት የሌለው ሲሆን ብዙ ጊዜ የሚያቀርቧቸውን የቁርዓን ጥቅሶች አብረን እንመልከት::

ስለመጽሐፍ ቅዱስ መበላሸት በቀዳሚነት ከሚጠቀሱት ጥቅሶች ሱራ 4:46 አንዱ ነው:: እንዲህም ይነበባል:- «ከነዚያ ይሁዳውያን ከሆኑት ሰዎች ንግግሮችን ከስፍራዎቹ የሚያጣምሙ አልሉ፤ ሰማንም አመጥንም፤የማትሰማም ስትሆን ስማ ይላሉ፤ በምላሶቻቸውም ለማጣመምና ሃይማኖትንም ለመዝለፍ ራኢና ይላሉ፤...::» በዚህ ክፍል አይሁዶች በመጽሐፉ ያልተጻፈውን እንዳለ አድርገው ያስተምራሉ፤ ምላሶቻቸውንም ያጣምማሉ ሲል ቃሉን ሲያነቡ አሳስተው ያነባሉ ማለት እንጂ ቃሉን አውጥተው

ሌላ ይጨምራሉ ማለት አይደለም:: በጽሑፍ ደረጃ መቀየር ይቅርና አይሁዶች በመጽሐፉ ያልነበረውንስ ያነቡ ነበር ወይ? በእርግጠኝነት መናገር ያዳግታል:: ምክንያቱም በዚያን ጊዜ በአረብያ ምድር የአረብኛ መጽሐፍ ቅዱስ ስላልነበረ መጣመም አለመጣመሙን ነብዩ መሐመድ ሊያውቁ የሚችሉበት አጋጣሚ በጣም የጠበበ ነበር:: ነብዩ መሐመድ እብራይስጥ ወይንም ግሪኩን ስለማያውቁ አይሁዶች ለአንድ ቃል ሌላ ተለዋጭ ቃላትን ሲጠቀሙ ንባቡን እንደማጣመም ወስደውታል እንጂ በዚህም ሆነ በዚያ ይህ የቁርዓን አንቀጽ የሚኮንነው የአነባበብ ችግር እንጂ መጽሐፉን በጽሑፍ ደረጃ መቀየሩን አይደለም:: የተወቀሱት አንባቢዎች ናቸው እንጂ መጽሐፉ ተበላሽቷል አልተባለም::

በሁለተኛነት የሚቀርበው የቁርዓንን ጥቅስ ሱራ 2:75 ነው:: ክፍሉም እንዲህ ይነበባል፡- «/ይሁዶች/ከነሱ የኾኑ ጭፍሮች የአላህን ቃል የሚሰሙና ከዚያም ከተረዱት በኋላ እነርሱ እያወቁ የሚለውጡት ሲሆኑ ለናንተ ማመናቸውን ትከጅላላችሁን?»በመጀመሪያ ደረጃ የአላህን ቃል የሚለው በዚህ አውድ መሠረት የቁርአንን መልዕክት እንጂ መጽሐፍ ቅዱስን አይደለም:: ስለዚህ ነብዩ መሐመድ በመዲና ቆይታቸው ከአይሁድ የተወሰኑ ቡድኖች የነብዩን መልዕክት ሰምተው አምነናል እያሉ ያታልሉ ነበር:: ነገር ግን ከነብዩ ሲለዩ የሰሙትን መልዕክት አጣምመው ያስተምራሉ:: የአረብኛውም ቁርአን ቀይረውታል የሚለው የአላህን ንግግር

- ከለም አሳህ /                /እንጂ መጽሐፉን
- ኪታብ /                / አይደለም:: ስለዚህ ይህንን ጥቅስ

የሚያስተምረው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ መበላሸት ሳይሆን ከነብዩ መሐመድ አፍ ስለሰሙት ንግግር ነው::

በሦስተኛ ደረጃ የሚነሳው ጥቅስ ሱራ 5:13-14 ነው:: ክፍሉም እንዲህ ይላል « ... ልቦቻቸውንም ደረቆች አደረግን ቃላትን ከስፍሮቻቸው ይለውጣሉ:: ...ከነዚያም እኛ ክርስቲያኖች ነን ካሉት የጠበቀ ቃል ኪዳናቸውን ያዝን:: በርሱም ከታዘዙት ነገር ፊንታውን ተዉ፤ ...::» በዚህ ክፍል አይሁዶችም ክርስቲያኖችም መጽሐፉን ሲያብራሩ ወይንም ትርጉሙን

(Meaning) ሲሰጡ የሌላውን እንደሚያስተምሩ ይገልጻል:: አብደላ የሱፍ ዓሊ ይህን ክፍል ሲያብራራ « አይሁዶችና ክርስቲያኖች በሚያስተምሩበት ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያሉትን ቃላት ሌላ ዓይነት ትርጉም እየሰጡ ያስተምራሉ ወይንም መዋል ለሌለባቸው ተግባር ያውላሉ ሲል ጽፎአል:: ይህም ንግግርን እንጂ በጽሑፍ ደረጃ ያለውን የእግዚአብሔር ቃል ማለቱ አይደለም:: ከዚህም የተነሳ ትክክለኛውን መልዕክት ረስተዋል የራሳቸውንም ሐሳብ ለመደገፍ ትክክለኛ ያልሆነ ማብራሪያ ይሰጣሉ » ሲል ጽፎአል (Yusuf Ali, 1999, p.250) ቁጥር 13 ላይ «ቃላትን» የሚለው «ከለም» የሚል የአረብኛ ቃል ስለተጠቀመ መጽሐፍ ቅዱስን በጽሑፍ ደረጃ ከመቀየር ጋር ምንም ዓይነት ግንኙነት የለውም::

ሱራ5:41/3:71 ተመሳሳይ ነገር ይናገራል:: ለእነዚህ ክፍሎች አብደላ ዩሱፍ አሊ ተመሳሳይ ማብራሪያ ሰጥቶአል:: ሱራ 3:77-78 ከላይ ከተጠቀሱት ክፍሎች ጋር ተመሳሳይነት አለው:: በአጠቃላይ ቁርአን ስለመጽሐፍ ቅዱስ መቀየር፣ መበላሸት ወይንም እርስ በርሱ መጋጨት ምንም ዓይነት መረጃ አይሰጥም:: ይልቁንስ ከፍ ብለን እንደተመለከትነው ስለ እውነተኛነቱ በእነዚህ የቁርአን አንቀጾች ከየትኛውም ጽሑፍ ይልቅ ጠንካራ ድጋፍ ይሰጣል::

## ለ/ ታሪካዊ መረጃዎች

### ስለመጽሐፍ ቅዱስ አለመበረዝ ታሪካዊ መረጃ ከቁርአን ጋር በንጽጽር የቀረበ፦

ሙስሊሞች አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ ለነብያትና ለሐዋርያት የተገለጠው አይደለም:: ብዙ ጊዜም ተለውጧል:: ስለ ዚህ ላለመለወጡ ምን መረጃ አላችሁ? ሲሉ ይጠይቃሉ::

በመሠረቱ ጥያቄው አግባብነት ያለው ይመስለኛል:: ነገር

ግን አንዳንድ ሙስሊሞች ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ ታሪካዊ፣ቁርዓናዊ ወይንም ሳይንሳዊ መረጃ ሳይኖራቸው የእግዚ አብሔርን ቃል ያንቋሽሻሉ:: ቀደም ብለን እንደተመለከትነው መጽሐፍ ቅዱስ ያልተበላሸ እንደሆነ ቁርዓንም መጽሐፍ ቅዱስም ያረጋግጣሉ:: ነብዩ መሐመድም በእርሳቸው ዘመን የነበረውን መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛና ያልተበላሸ እንደሆነ መስክረዋል፤ ተከታዮቻቸውንም እንዲያምኑበት በሱራ 4:136 አስተምረዋል:: ከዚህ በተጓዳኝ አሁን ያለው መጽሐፍ ቅዱስ በነብዩ መሐመድ ዘመንና ከዚያ በፊት ክርስቲያኖችና አይሁዶች ይጠቀሙበት የነበረው ነው:: በዚያን ጊዜ በተለያዩ ቋንቋዎች የተጻፉት መጽሐፎች በአሁኑ ጊዜ በክርስቲያኖች እጅ ይገኛሉ:: ከእነዚህም ውስጥ ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው:-[1]

1/ የአሌክሳንደሪያ ጽሑፍ (Codex alexandrinus) :- የተጻፈው በ5ኛው ክፍለ ዘመን ከእስልምና መጀመር አንድ መቶ አመት በፊት ነው:: አሁን በለንደን ብሪቲሽ ሙዝየም ውስጥ ይገኛል::

2/ የሲናይቲክስ ጽሑፍ (Codex sinaiticus):- ይህ ደግሞ በ4ኛው ክፍለ ዘመን የተጻፈ ሲሆን አሁን በብሪቲሽ ሙዝየም ይገኛል::

3/ የቫቲካነስ ጽሑፍ ( Codex vaticanus):- ከሁለቱ ይልቅ ረጅም እድሜ ያለው ሲሆን በአሁኑ ጊዜ በሮም የባተካን ላይብረሪ ይገኛል::

4/ የእብራይስጡ ማዘሬቲክ መጽሐፍ (The Hebrew massoretic text):- በእብራይስጥ ቋንቋ የተጻፈ ሲሆን በክርስቲያኖችም በአይሁዶችም እጅ አለ:: ከክርስቶስ ልደት በፊት የተጻፈ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው::

5/ የሙት ባሕር ጥቅልል ( dead sea scroll):- በሙት ባሕር አካባቢ በተደረገው የአርኪኦሎጂ ቁፋሮ የተገኘ መጽሐፍ ነው::

ይህም መጽሐፍ ቅዱስ ከክርስቶስ ልደት በፊት ሁለት መቶ ዓመታት እድሜ አለው::

6/ ሰፕቱጀንት:- ከእብራይስጥ ወደ ግሪክ የተተረጎመ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍ ነው:: ይህም መጽሐፍ የተጻፈው ከክርስቶስ ልደት ሁለት መቶ ዓመታት አስቀድሞ ነው::

7/ የላቲን ቩልጌት:- የሮማ ካቶሊክ ቤተክርስቲያን በ4ኛው ክፍለ ዘመን ከሰፕቱጀንትና ከጥንታዊ የግሪክ መጽሐፍት የተረጎመችው ነው::

እነዚህ መጽሐፍት ከመሐመድ ልደት ብዙ መቶ ዓመታት በፊት የተጻፉ ወይንም ከሌላ ቋንቋ የተተረጎሙ ናቸው:: ነብዩ መሐመድም ትክክለኛና ያልተበላሹ በማለት የተቀበለችው እነኚህ መጽሐፎች ናቸው:: አሁንም ያለምንም ዓይነት ችግር በእጅ ይገኛሉ:: ይዘታቸውም አሁን ካለው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር አንድ ዓይነት ነው:: ጽሑፎቹም ከበቂ በላይ ማስረጃዎች ናቸ ውና:: ማንም ሰው በዚህ ጉዳይ ጥርጣሬ ቢያድርበት ጽሑፎቹ ወዳሉበት ድረስ በመሄድ አሁን ካለው መጽሐፍ ቅዱስ ጋር ማስተያየት ይችላል:: በጥቂት ሰዎች መረጃ በሌለው መላ ምት ንግግር መሳሳት አይገባም:: ይልቁንስ እውነቱን በደንብ ለማወቅ ከፈለግን ቀጥሎ ያሉትን ጥያቄዎች ራሳችንን ልንጠይቅ ይገባናል:: እነማን ናቸው የቀየሩት? ለምንድነው የቀየሩት? የት በታ ወይንም በየትኛው የቤተክርስቲያን ጉባኤ? በስንት ዓመተ ምሕረት? ተቀየረ ከተባለስ የመጀመሪያው መጽሐፍ ቅዱስ የት ነው ያለው? የትኞቹ ክፍሎች ናቸው የተቀየሩት? ተቃዋሚዎች ለእነዚህ ጥያቄዎች ሁሉ የተጨበጠ መረጃ ማቅረብ አይችሉም:: መጽሐፍ ቅዱስን የሚቃወሙት እንዲሁ በጭፍን ነው::

የተወሰኑ ሙስሊሞች ቁርአን ስህተት ሊኖረው እንደሚችል ቢስማሙም አንዳንዶች ግን ምንም ዓይነት ስህተት የሌለበት፣ ሲጻፍም ያለ እንከን ተከትቦ እስካሁን እንደደረሰ ያስተምራሉ:: በተለይም አቶ ኡመር አርሲ በቅርቡ «ታላቅ ምክር

ለአዲሱ ትውልድ» በሚለው መጽሐፋቸው ከገጽ 6-10 ስለ ቁራአንና ስለ መጽሐፍ ቅዱስ በንጽጽር አቅርበዋል:: በገጽ 6 ላይ ሱራ 41:42 እና ሱራ 4:82 በመጥቀስ የቁርአንን እውነተኛነት ሲጽፉ በተቃራኒው ከጌርሃርድ ኔልስ መጽሐፍ በመጥቀስ የመጽሐፍ ቅዱስን ብልሽት ለማሳየት ሞክሮአል:: ከጌርሃርድ ኔልስ የተወሰደው ሐሳብ ከእንግሊዘኛው ወደ አማርኛው በትክክል ካለመተርጎሙም በላይ ትክክለኛ ተቃውሞ አይደለም:: የቁርአንን ማንነት ከግምት ውስጥ ያላስገባ ተቃውሞ ስለሆነ ከዚያ በፊት አቶ ኡመር ባነሱት ርዕስ ቁርአንን መፈተሽ ይኖርበታል::

የተለያዩ የቁርአን፣የሐዲስና ሌሎች እስላማዊ ጽሑፎች ቁርአን ተሰብስቦ እስኪጻፍ ድረስ በብዙ ችግሮች ውስጥ እንዳለፈ ያስረዳሉ:: አንዳንድ ሙስሊም ሊቃውንቶች አሁን ያለው ቁርአን በመጀመሪያ ለነብዩ መሐመድ የተገለጠው መልዕክት ነው ብሎ ለመቀበል ሲቸገሩ ሌሎች ግን አላህ ቃሉን ይጠብቃል በሚል ጭፍን እምነት ሽንጣቸውን ገትረው ይከራከራሉ:: ከቁርአን ብንጀምር በሱራ 2:106 ነብዩ መሐመድ የተወሰኑ የቁርዓን አንቀጾችን እንደረሱና ወደፊትም ሊረሱ እንደሚችሉ ተጽፎአል:: በዚህ ጉዳይ ከሌሎች ለቀረበላቸው ጥያቄ ምላሽም አላህ አንዱን መልዕክት ቢያስረሳ ብጤውን ወይንም የተሻለውን ያመጣል ሲሉ ጽፈዋል:: ነገር ግን አላህ አንዱን መልዕክት አስረስቶ ሌላውን ማምጣት ለምን አስፈለገው? እርሱም እንደነብዩ የመጀመሪያውን መልዕክት ረስቷል ማለት ነው? የመልዕክቱ ምንጭ ሁሉን ቻይ አምላክ ከሆነ እንዲህ ሊያደርግ አይችልም:: ደግሞ በእግዚአብሔር ቃል ውስጥ የተሻለ ወይም ያነሰ የሚባል እንዴት ይኖራል?

በተጨማሪም የነብዩ መሐመድ ተከታዮች ተመሳሳይ ችግር እንደገጠማቸው የታመኑ የሐዲስ ሪፖርቶች ያስረዳሉ:: «ሐዲስ» ማለት የነብዩ መሐመድ ንግግሮች፣ አባባሎችና ተግባሮች ስብስብ ነው:: በእነዚህ መረጃዎች መሠረት ከነብዩ መሐመድ ሞት በኋላ በተለይም በአቡ በክር ዘመን «ያማማህ» በተሰኘው የጦር ግንባር ቁርአንን በአእምሮአቸው ይዘው የነበሩ ሰዎች በብዛት

መሞታቸው ለቁርዓን ተሰብስቦ መጻፍ ዋንኛው ምክንያት ነው:: በዚህም ጊዜ በካሊፍ አቡ በክር ትዕዛዝ ዘይድ ኢብን ሣቢት የተባለው ሰው ቁርጥራጭ የቁርዓን አንቀጾችን ሰብስቦ ጽፎአል:: የሰበሰበውም በሰሌን፣ በድንጋይ እና በሌሎችም ዕቃዎች ላይ በነብዩ ዘመን ከተጻፈበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከነብዩ ተከታዮች አእምሮ በመልቀም ነው:: የተጻፈውም ቁርአን ሐፍሳ በምትባለው በነቢዩ መሐመድ ሚስት እጅ እንዲቀመጥ ተደርጓል:: ( sahih al-Bukhari, vol,6.p.478) እዚህ ላይ ቆም ብላችሁ አስቡ ነብዩ እንኳን ከረሱ ተከታዮቻቸው ረጃጅምም ሆኑ አጫጭር የቁርአን መልዕ ክቶች ምንም ሳያዛንፉና ሳይረሱ ለብዙ ዓመታት እንዴት በአእምሯቸው ይዘው ሊቆዩ ይችላሉ?

በሌላ አንጻር ደግሞ የነብዩ መሐመድ የቅርብ ረዳት የነበሩ ሦስት ሰዎች ማለትም አብደላህ ኢብን ማሱኡድ፣ ሳሊም እና ኡቤይ ኢብን ካዕብ የየራሳቸው ሦስት ቁርዓኖች አዘጋጅተው ነበር::[2] ነብዩ በሕይወት ሳሉ ማንኛውም ሰው ስለቁርዓን ለመማር ቢፈልግ እነርሱ መጠየቅ እንዳለበት በማሳሰብ ታማኝነታቸውን አረጋግጠውላቸው ነበር:: ከዚህ በተጨማሪ ሌሎችም ሰዎች በተመሳሳይ ሁኔታ የየራሳቸው ቁርአን አዘጋጅተው ነበር:: ከነዚህም ውስጥ አሊ፣ አቡ ሙሳ እና አናስ ኢብን ማሊክ ይገኙበታል[3] ስለዚህ ከእነዚህ ቁርዓኖች የትኛው ነው ትክክለኛ? ልዩነት ካለ ጭቅጭቅ አይቀርምና ከነቢዩ ሞት ከ12 ዓመታት በኋላ ችግሩ እየተገለጠ መጥቶ በተለያዩ ግዛቶች ባሉ ሙስሊሞች መካከል ክርክር ተነሳ:: በዘመኑ ገዥ የነበረው ካሊፍ ኡስማን በሙስሊሞች መካከል ቁርዓንን በተመለከተ የተነሳውን ክርክር ሲሰማ ያልተጠበቀ አደገኛ ውሳኔ ወሰደ:: ይህም ዘይድ ኢብን ሣቢት ለሁለተኛ ጊዜ የመጨረሻ የሆነውን ቁርአን በቁረይሾች አረቢኛ እንዲያዘጋጅ አዘዘው::[4] ዘይድም ቀድሞ አዘጋጅቶት የነበረውን ቁርአን ከሐፍሳ እጅ በመውሰድ የመጨሻው ቁርዓን ( mus-haf) ጻፈ:: በዚህ ሂደት ውስጥ የቁርአን እጣ ፈንታ የወደቀው በዘይድና በተባባሪዎቹ እጅ ነው:: ተጽፎ ካለቀም በኋላ ካሊፍ ኡስማን ሌሎችን ቁርዓኖች እንዲቃጠሉ አዘዘ:: ስለ ቁርዓን አሰባሰብና በውስጡ ስለተፈጠሩ

ግጭቶች የአማርኛው ቁርዓን በገጽ 10 ላይ እንዲህ ያብራራ ዋል:- " ዳግመኛ ኸሊፋ ኡስማን በ25ኛው ዓመት ስደት ባነባበቡ ግጭት ስለተገኘበት ከአራት የቁርዓን ሊቃውንት በተከናወነ ጉባኤ የቃላቱን አጻጻፍ ያለነጥብ ለየንባቡ ተስማሚ አድርገው በመጀመሪያው አወራረድ መሠረት የሱራዎቹንም ተራ ጠብቀው ሰበሰቡት፣ ኸሊፋውም በአምስት ኮፒዎች አስጽፎ አንዱን ለራሱ አስቀርቶ አራቱን ለመካና ለደማስቆ፣ለበስራ፣ለኩፋ ከተሞች ልኮ ማንኛውም ሰው ከነዚህ ብቻ እንዲገለብጥ አድርጎ የቀረውን ስለ አቃጠለው ቁርአን አንድነቱን ጠብቆ ይኖራል እስከ አሁን ምንም መለዋወጥ አልደረሰበትም:: " ዘይድ ካዘጋጀው ቁርአን ጋር አንድ ዓይነት ይዘት ካላቸው ለምን ተቃጠሉ?፣ ተመሳሳይ ይዘት ከሌላቸውስ ትክክለኛው ቁርአን የዘይድ ወይንም የሌሎቹ ይሁን በምን ይታወቃል? የቁርአንን አንድነት የሚጠበቀው እርስ በርሳቸው የሚጋጩትን የቁርአን ክፍሎች ወይንም ዘይድ ካዘጋጀው ቁርአን ጋር የሚጋጩትን ቁርአኖች በማቃጠል ነውን? ከነብዩ መሐመድ ጋር የነበሩ ታማኝ የተባሉት የነብዩ መሐመድ ተከታዮች የጻፉዋቸውን ቁርአኖች ተቃጥለው ሳሉ ቁርአን መለዋወጥ አልደረሰበትም ማለት ይቻላልን?

በእስልምና የመጀመሪያዎቹ ዘመናት የነብዩ ተከታዮች ከቁርዓን ብዙ መልዕክቶች እንደረሱ አል-ሱዩቲ የተባለው ሐዲስ አብደላ ኢብን ኡመርን ጠቅሶ እንደሚከተለው ዘግቦታል::" Let none of you say 'I have aquired the whole of qur`an.' How does he know what all of it is when much of the quran has disappeared? Rather let him say ' I have a quired what has survived.'" ( as -suyuti, al-Itfan tiiulum al-qur`an p.524 [5]

ወደ አማርኛው ሲተረጎም እንደሚከተለው ነው:-

«ማንም እንዲህ አይበል" ሙሉውን ቁርአን አግኝቻለሁ ' አብዛኛው ቁርአን ጠፍቶ ሳለ ሙሉ ቁርአን መሆኑን እንዴት ሊያውቅ ይችላል? ይልቁንስ እንዲህ ይበል" እኔ ያገኘሁት የቀረውን /ከመጥፋት የተፈረውን /ነው::»

ከዚህ በተጨማሪ ከቡሐሪ ሐዲስ ቀጥሎ ታማኝ በሚባለው ሐዲስ ሳሂሁ - ሙስሊም በሁለተኛው ጥራዝ ገጽ 501 የጠፉ ሱራዎች እንዳሉ አቡ ሙሳ አል አሻሪ ጠቅሶ እንዲህ ተጽፎአል::

«We used to recite a surah which resembled in length and severity to surah Bara`at. I have, rember out of it: ' If there were two valleys full of riches, for the son of Adam, he would long for a third valley, and nothing would fill the stomach of the son of Adam but dust." ( sohih- muslim v.2.501)

በዚህ የሐዲስ ሪፖርት እንደምናየው አቡ ሙሳ አል-አሻሪ ከአንድ ሱራ /ምዕራፍ/ አንድ ዐረፍተ ነገር ሲቀር ሁሉንም ረስተዋል:: በተመሳሳይ የሐዲስ ክፍል አቡ ሙሳን ጠቅሶ የተረሳ የቁርአን ሱራ እንዳለ እንዲህ ይገልጻል:-

" And we used to recite a surah which resembled one of the surahs of Musabbihat, and I have forgotten it, but remember ( this much) out of it. ' O people who believe, why do you say that which you do not practice' ( 61:2) and ' that is recorded in your necks as a witness ( against you) and you would be asked about it in the day of Resurrection."' ( 17:13) ( sahih- Muslim,v.2,.501).

በዚህ ክፍል አቡ ሙሳ ከአንድ ምዕራፍ /ሱራ/ሁለት ጥቅሶችን ሲያገኙ ቀሪዎቹ እንደተረሱ ተናግረዋል:: እነዚህም ሁለት ጥቅሶች በሱራ 61:2 እና በ17:13 ውስጥ ተጽፈው እናገኛቸዋለን:: ቀሪውን የቁርአን መልዕክት ሳይገኝ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ተረስቷል:: ቡሐሪ የተሰኘውም ሐዲስ ካሊፍ ኡመርን ጠቅሶ ከዚህ ቀጥሎ ያለውን አረፍተ ነገር ድሮ በቁርአን ውስጥ እንደነበረ በኋላ ግን እንደጠፋ ዘግቧል:

O people! Do not claim to be the offspring of other than

your fathers, as it is disbelief on your real part that you claim to be the offspring of other than your real father. ( sahih al-Bukahri, v.8, p.540)

ከቁርአን የተወሰነው መልዕክት ከጠፋ፤ ወይንም ከተረሳ፣ እንዲሁም በአሰባሰቡም ላይ ችግር ካለበት በመጀመሪያ ለነብዩ የተገለጠው መልዕክት አሁን በእጅ አለ ብሎ መናገር እንዴት ያስደፍራል? ስለቁርአን ምንም ዓይነት መጥፎ ነገር እንዳይነገር የሚከለከለው ለምን ይሆን? ሙስሊም ወንድሞቼና እህቶቼ እግዚ አብሔር የሰጣችሁን አእምሮአችሁ/ እውነትን ለማወቅና ትክክለኛውን መንገድ ለመከተል እንድትጠቀሙበት አበረታታችኋለሁ:: ለሰዎች እውነት የሚመስሉ ብዙ መንገዶች አሉ መጨረሻቸው ግን ሞት ነው:: ወደ ዘላለም ሕይወት የሚወስድ እውነተኛ መንገድ አለ፤ እርሱም አል መሲህ ኢሳ ነው:: በዮሐ.14:6 ኢሳ ሲናገር " እኔ መንገድና እውነት ሕይወትም ነኝ፤ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም::" አለ:: እግዚአብሔር ለሰው ዘር ሁሉ ያለምንም ድካምና ጥረት ከእግዚአብሔር ምሕረት ብቻ የተነሳ የደህንነትን መንገድ አዘጋጅቶልናል::

ከእኛ የሚጠበቀው ማመንና መከተል ብቻ ነው:: እንዲሁም ኢየሱስ /ኢሳ/ በዮሐንስ ወንጌል 3:36 እንዲህ ብሏል « በልጁ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው፤ በልጁ የማያምን ግን የእግዚ አብሔር ቁጣ በእርሱ ላይ ይኖራል እንጂ ሕይወትን አያይም::» ሌላ መንገድ የለም፤ መንገዱ ይህ ብቻ ነው፤ በዚህ እንመላለስ::

## ሐ. ከኦሪትና ከወንጌላት ውጪ ሌሎች መጽሐፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አይደሉምን?

ጥቂት ሙስሊሞች ከኦሪት /ተውራት/ እና ከወንጌላት /ኢንጂል/ ውጪ የሌሎች ነብያትና ሐዋርያት መጽሐፍት የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍሎች አይደሉም የሚል አስተያየት በተቃውሞ

መልክ ያቀርባሉ:: አሁን ያሉት ኦሪትና ወንጌላት ከጥንቶቹ ጋር አንድ ዓይነት አይደሉም ይላሉ::

ለዚህ አባባል ምንም ዓይነት መጽሐፍ ቅዱሳዊ፣ታሪካዊ ወይንም ቁርአናዊ መረጃ የለውም:: አሁን ካለው የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ውጪ ሌላ ይዘት ያለው መጽሐፍ የነበረበት ዘመን በዓለም ታሪክ አይታወቅም:: አንዳንድ ተቃውሞዎች ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ላይ የተመሠረተ ነው:: ቁርአንም ከኦሪት /ተውራት/እና ወንጌላት /ኢንጂል/ ውጪ ለሌሎች ነብያት መጽሐፍትን እንደተሰጡ በሱራ 2:136 እንዲህ ተጽፎአል:-

«በአላህና ወደኛ በተወረደው /ቁርአን/ ወደ ኢብራሂምም ወደ እስማኤልና ወደ ኢስሐቅም ወደ ያዕቆብና ወደ ነገዶቹ በተወረደው በዚያም ሙሳና ኢሳ በተሰጡት በዚያም ነብያት ሁሉ ከጌታቸው በተሰጡት በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን...::»

በዚህ የቁርአን አንቀጽ መሠረት የመጽሐፍ ቅዱስ መጽሐፍት ኦሪትና ወንጌላት ብቻ ሳይሆኑ በተለያዩ ነብያት እና ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ እንደሆነ ያረጋግጣል:: ቁርአን የመጽሐፎቹ ብዛትና ይዘት ምንም የሚለው ነገር የለም:: ከጥንት ጀምሮ የነበረው የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ቁጥር 39 ሲሆኑ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ሲመላለስ በነበረበት ጊዜ ከእነዚህ መጽሐፍትም እየጠቀሰ ያስተምር ነበር:: የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት ደግሞ 27 ሲሆኑ በእግዚአብሔር መንፈስ መሪነት በኢየሱስ ሐዋርያትና በቅርብ ረዳቶቻቸው የተጻፉ ናቸው:: በአጠቃላይ መጽሐፍት ቅዱስ 66 መጽሐፍ በውስጡ የያዘ ሲሆን በቁርአን በሱራ 2:136 እንደተጻፈው በእስራኤል ነቢያት፣ ሐዋርያት እና ሌሎች ቅዱሳን ሰዎች የተጻፈ ነው:: ብዙ መጽሐፍት ቢሆኑም ምንም ዓይነት የሐሳብ ግጭት አይታይባቸውም:: ነብዩ መሐመድም የእግዚአብሔር ቃል ናቸው ሲሉ የሚናገሩት እነዚህ 66ቱ መጽሐፍት ናቸው:: እነዚሁ መጽሐፎች በነብዩ ዘመን በክርስቲያኖች እጅ የነበሩ

ናቸው:: ስለዚህ ቀደም ብሎ የተነሳው ተቃውሞ ከቁርአንና ከታሪክ እውነታ ጋር የሚጋጭ ስለሆነ ሊስተካከል ይገባዋል::

## መ. የበርናባስ ወንጌል ትክክለኛ ወንጌል ነውን?

ሙስሊሞች እውነተኛው ወንጌል የበርናባስ ወንጌል ብቻ ነው ይላሉ:: ሌሎች ወንጌላት የተቀየሩ ፣የተበላሹና እውነተኛነት የጎደላቸው ሲሉ ያጣጥላሉ:: እነርሱ እንደሚሉትም የበርናባስ ወንጌል ስለ ክርስቶስ አለመሰቀል ፣ ስለ ነብዩመሐመድ መምጣት፣ ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅ እንዳልሆነ ነገር ግን የእስልምና ነብይ ብቻ እንደሆነ ያስተምራል:: በተጨማሪም ኢየሱስ መሲህና አምላክ እንዳልሆነ ይናገራል:: ስለዚህ ሙስሊሞች የበርናባስ ወንጌል ክርስቲያኖች ከእምነታቸው ጋር ስለሚጋጭ አውጥተውታል ይላሉ:: እውነተኛው ለኢየሱስ የተሰጠው ወንጌል /ኢንጂል/ ነው ሲሉም ይከራከራሉ::

በቅድሚያ ባርናባስ ከጳውሎስ ጋር ወንጌልን በሕብረት ያገለገለ ሰው ነው:: ሐዋ.13:1-39 እና 11:26-30:: ባርናባስ የኖረውም እስልምና ከመጀመሩ 500 ዓመታት በፊት ሲሆን አሁን ያለው የበርናባስ ወንጌል ጸሐፊም አይደለም:: ሙስሊሞች ያቀረቡት መጽሐፍ በ14ኛው ክፍለ ዘመን የቁርአን ትምሕርቶችና የእምነቱ አስተምህሮዎች ከኢየሱስ ጋር ለማያያዝ የተደረገ ፈጠራ ነው:: በሌላ በኩል ደግሞ ክርስቲያኖች የእስልምናን እምነት እንዲቀበሉ የተወጠነ ዘዴ ነው::

የመጽሐፉን አጠቃላይ ታሪክ ስንመለከት ለመጀመሪያ ጊዜ የተጻፈው በጣሊያንኛ ቋንቋ ነው:: ፀሐፊውም በግዳጅ ወደ ክርስትና የተቀየረ ስፔናዊ ሙስሊም ነው:: ከዚያ በኋላ አባ ማሪኖ የተባለ ቄስ ባርናባስ ጽፎታል የሚለውን ሐሳብ እንዳሰራጨ ይታመናል::

ስፔናዊው ወታደር ወደዚህ ድርጊት የገባው በግዳጅ ክርስትና

እንዲቀበል ስለተደረገ ለብቀላ የተጠቀመበት መንገድ ነው:: አባ ማሪኖ ደግሞ ወደዚህ ድርጊት የተገፋፋው ለብዙ ዓመታት አገልግሎ የማዕረግ እድገት ስላልተሰጠው ነው:: እርሱም ቤተክርስቲያን ለመበቀል የተጠቀመው ዘዴ ነው:: ቄሱ ከዚያ ወደ እስልምና ሃይማኖት ተቀይሯል:: ባርናባስ ግን ጣሊያንኛ ተናጋሪ አልነበረም:: እርሱ ቢጽፈው ኖሮ ሊሆን የሚችለው በግሪክኛ ወይንም በእብራይስጥ ነው:: ቋንቋው በራሱ የመካከለኛው ዘመን ፈጠራ እንደሆነ ያሳያል:: በኋላም ወደ ስፓኒሽ የተተረጎመ ሲሆን በጣሊያንኛው መጽሐፍ ህዳጉ ላይ ያሉ ጽፎች በአረብኛ የተጻፉ ናቸው:: የመጽሐፉ የእንግሊዘኛ ትርጉም በ1907 በሉንስዴል እና ለውራንግ ተዘጋጠጅቷል:: 100,000 የሚጠጉ ኮፒዎች በፓኪስታን ታትመው ተሰራጭተዋል:: የአባ ሞሪኖ በአጠቃላይ የባርናባስ ወንጌል ና የስፓኒሽ ሙስሊም ሰው ፈጠራ ውጤት ነው::[6] ለዚህም የተለያዩ መረጃዎች አሉ::

ሀ/ በሉቃስ 17:16 ኢየሱስ ከፈወሳቸው አስር ለምጻሞች ወደ ጌታ የተመለሰው ሳምራዊ እንደሆነ የሉቃስ ወንጌል ያስረዳል:: ነገር ግን የባርናባስ ወንጌል እስማኤላዊ ነበር ይላል:: ( Barnabas 70)

ለ/ የባርናባስ ወንጌል ከቁርአንም ከመጽሐፍ ቅዱስም ጋር ይጋጫል:: ለምሳሌ ኢየሱስ መሲህ አይደለም፤ እርሱ ስለመሲሁ መምጣት ሊያበስር የተላከ ነብይ ነው ይላል:: ( Batnabas 42 እና 82) ነገር ግን ቁርአን 11 ጊዜ ኢየሱስ መሲህ ነው ሲል ያስተምራል:: ከነዚህም ውስጥ ሱራ3:45 ይገኝበታል::

ሐ/ ከሌላ የቁርአን አንቀጽ ጋር የሚጋጭ ትምሕርት አለው:: በሱራ 19:23 ማሪያም ኢየሱስን ስትወልድ ተጨነቀች ይላል:: ነገር ግን የባርናባስ ወንጌል ያለምንም ጭንቀት እንደወለደች ያስተምራል:: ( Barnabas 3)

መ/ የባርናባስ ወንጌል ኢየሱስ ሰዎች ካልተገረዙ አይድኑም ብሎ አስተምሯል ሲል ዘግቧል:: ነገር ግን ጳውሎስም ባርናባስም

የተቃወሙት ትምሕርት ነው::-ሐዋ.15:1-29፣ ገላ.5:6-7

ሠ/ ነብያት፣ ሐዋርያት፣ መላዕክቶች እንዲሁም ኢየሱስ ራሱ ያስተማሬን የክርስቶስ የእግዚአብሔር ልጅነቱ የባርናባስ ወንጌል ተቃውሞታል::

ረ/ የባርናባስ ወንጌል ፀሐፊ ከቁርአን እና በ13ኛው መቶ ክፍለ ዘመን በጣሊያናዊው ዳንቴ ከተጻፈው " the divine comedy " ከሚለው ጽሑፍ የተወሰዱ ሐሳቦች በውስጡ ይዟል:: በ1ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የኖረው ባርናባስ ከነዚህ ጽሑፎች ጋር ምንም ግንኙነት የለውም::

በአጠቃላይ የባርናባስ ወንጌል በመካከለኛው ዘመን በስፓኒሽ ሙስሊም ሰው የተቀነባበረ መጽሐፍ ነው:: እርሱም የእስልምና ሃይማኖት እውነተኛና መገለጡም የመጣው ከእሥራኤል አምላክ ቅዱስ እግዚአብሔር እንደሆነ ለማስመሰል ያዘጋጀው ተረት ነው::